የሰ.መ.ቁ.230493

ጥቅምት 2 ቀን 2016 ዓ.ም

ዳኞች፡- 1. ብርሃኑ አመነዉ

2. ረታ ቶለሳ

3. በዕዉቀት በላይ

4. ቀነዓ ቂጣታ

5. ኑረዲን ከድር

አመልካች.....ንብ ትራንስፖርት አ.ማ ጠበቃ ተከተል ድሃ - ቀረቡ

ተጠሪ.....1. የኢትዮጵያ መድህን ድርጅት

2. አቶ ገብረሀዋርያት ገብረመድህን ገብረማርያም } የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ይህ የጉዳት ካሳ ክርክር የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን፣ የአሁን አመልካች የሥር 2ኛ ተከሳሽ፣ የአሁን 1ኛ ተጠሪ የሥር ከሳሽ፣ የአሁን 2ኛ ተጠሪ የሥር 1ኛ ተከሳሽ ሆኖ ሲከራከሩ ነበር፡፡ ይህ ጉዳይ ለዚህ ችሎት ሊቀርብ የቻለዉ አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.282450 ሚያዚያ 07 ቀን 2014 ዓ.ም የሰጠዉ ብይን መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልን በማለት በማመልከቱ ነዉ፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ ከሳሽ በሥር ፍ/ቤት ባቀረበዉ ክስ፡ ከሳሽ የደንበኛዉ የመከላከያ ሚኒስቴር የሆነ የሠ.ቁ.መ.ከ. 06890 ለአንድ አመት የሚቆይ ጠቅላላ የመድህን ሽፋን የሰጠን ሲሆን፣ የ1ኛ ተከሳሽ ተሽከርካሪ የሠ.ቁ. ኮድ 3-15499 ኢት እና የ2ኛ ተከሳሽ ተሽከርካሪ የሠ.ቁ. ኮድ 3-03984 ኢት ተሣቢ በደንበኛዬ ተሽከርካሪ ላይ የግጭት አደጋ የደረሱ በመሆኑ፣ ከሳሽ ተሽከርካሪዉን ለማስጠገን ብር 181823.03 ያወጠን ስለሆነ፣ የብሔራዊ የኢትዮጵያ ኢንሹራንስ ኩባንያ ብር 96430 ለከሳሽ የከፈለ ቢሆንም ቀሪ ብር 83712.89 ስላልተከፈለን ተከሳሾች ይህን ገንዘብ በአንድነትና በነጠላ እንዲከፈለን በማለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡

ማ ሰታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለማንዛቤ አንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

1ኛ ተከሳሽ በዚህ ክስ ላይ ይህን ጉዳይ ፎርም ሞልቼ ለኢንሹራንስ ያስተላለፍኩኝ ስለሆነ ክስድስት ዓመት በኋላ ሊጠየቅ አይገባም፤ የተጎደዉ ተሽከርካሪ ጨረታ ወጥቶ ማሰራት ነበረብን በራሳቸዉ ጊዜ ኢንሹራንስ ወስደዉ አሰርተዉ ገንዘብ ክፈሉን ማለት ተገቢ አይደለም በማለት ተከራክሯል፡፡

2ኛ ተከሳሽ በክሱ ላይ ባቀረበዉ መልስ በከሳሽ ደንበኛ ተሽከርካሪ ላይ ጉዳት ያደረሰዉ የ2ኛ ተከሳሽ ተጎታቹ ተሳቢ ሳይሆን ከፊት የነበረዉ የ1ኛ ተከሳሽ ተሽከርካሪ ነዉ፤ ተሳቢዉን 1ኛ ተከሳሽ በኪራይ የወሰደዉ በመሆኑ 2ኛ ተከሳሽ ኃላፊነት የለብንም፤ ተከሳሾች የየግላችን ተሽከርካሪ በመሆኑ በአንድነትና በነጠላ ኃላፊነት ልንባል አይገባም በማለት ተከራክሯል፡፡

ከዚህ በኋላ የሥር ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር በመመርመር በሰጠዉ ዉሳኔ የከሳሽ ደንበኛ መከላከያ ሚኒስቴር ተሽከርካሪ በሆነዉ የሠ.ቁ.06890 መካ ላይ በተከሳሾች ተሽከርካሪዎች ግጭት አደጋ ጉዳት የደረሰ መሆኑ ተረጋግጧል፤ የሠ.ቁ.3-15499 ኢት የሆነዉ ተሽከርካሪ የ1ኛ ተከሳሽ ሲሆን የሠ.ቁ.3-03984 ኢት ተሳቢ የሆነዉ ደግሞ የ2ኛ ተከሳሽ ንብረት ነዉ፡፡ በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከተማ ፖ/ሊስ መምሪያ በጻፈዉ የባለሙያ ማብራሪያ በከሳሽ ደንበኛ ተሽከርካሪ ላይ ጉዳት የደረሰዉ በተከሳሾች ጥፋት መሆኑን፣ ለደረሰዉ ጉዳት ኃላፊ እንደሚሆን በፍ/ብ/ሕ/ቁ.2081 (1) (2) ሥር ተመልክቷል፤ 2ኛ ተከሳሽ ወደዉና ፈቅደዉ በኪራይ ለ1ኛ ተከሳሽ ያስተላለፈዉ በመሆኑ ኃላፊነታቸዉን ቀሪ አያደርገዉም፤ ተከሳሽ በከሳሽ ደንበኛ ተሽከርካሪ ላይ ለደረሰዉ ጉዳት ኃላፊነት ስላለባቸዉ ከሳሽ መኪናዉን ለማስጠገን ያወጣዉን ወጪ ለመክፈል ተከሳሾች በአንድነት ኃላፊነት ያለባቸዉ በመሆኑ በአንድነት ብር 83712.89 ለከሳሽ ከ9% ወለድ፣ የዳኝነት እና ከተለያዩ ወጪዎች ጋር እንዲተኩለት በማለት ወስኗል፡፡

የሥር 2ኛ ተከሳሽ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበ ቢሆንም ፍ/ቤቱ ይግባኙን በትዕዛዝ ዉድቅ በማድረግ የሥር ፍ/ቤትን ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ነዉ፡፡

የአሁን አመልካች ሐምሌ 4 ቀን 2014 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ፡ አመልካች የራሱ ንብረት የሆነዉን የሰ.ቁ. ኮድ 3-03984 ኢት የሆነዉን ተሳቢ ተሽከርካሪ ለ2ኛ ተጠሪ ያከራየዉ መሆኑ ያልተካደና በ1ኛ ተጠሪ ደንበኛ ተሽከርካሪ ላይ ጉዳት በደረሰበት ወቅት ተሳቢዉ በ2ኛ ተጠሪ እጅ የነበረ በመሆኑ፣ 2ኛ ተጠሪ ተሳቢዉን ለግል ጥቅሙ ሲገለግልበት የነበረ በመሆኑ፣ ጉዳቱም የደረሰዉ በ2ኛ ተጠሪ ጥፋት ስለሆነ የመጨረሻ ኃላፊነት ያለበት የአሁን 2ኛ ተጠሪ ሆኖ ሳለ፣ የፍ/ብ/ሕ/ቁ.2082 (1) (2) እና ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ.55228 ላይ ከሰጠዉ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ዉሳኔ በሚቃረን ሁኔታ አመልካችም ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ያልተነጣጠለ ኃላፊነት አለባቸዉ የተባለዉ የህግ ስህተት ያለበት ነዉ፡፡ አመልካችም በዚህ ጉዳይ ኃላፊነት አለበት የሚባልበት ሕጋዊ ምክንያት ካለ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ባልተነጣጠለ ኃላፊነት እንዲንከፍል መወሰን የለበትም፣ እያንዳንዳችን በተሽከርካሪያችን ድርሻ ልክ ነዉ መወሰን ያለበት፡፡ በመሆኑም የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ዉሳኔ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ እንዲሻርልን፣ ይህ ካልሆነ እያንዳንዳችን በግል ተሽከርካሪያችን ድርሻ ልክ ኃላፊ እንዲሆን በማለት አመልክቷል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን በማየት ፣የአሁን አመልካች ኃላፊነት አለበት የተባለበት አግባብ ከፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ.55228 ከሰጠዉ ዉሳኔ አንጻር ለማጣራት ሲባል የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል በማለት ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡ ባዘዘዉ መሰረት 1ኛ ተጠሪ በ21/4/2015 ዓ.ም የተጻፈ መልስ አቅርቧል፡፡ የመልሱም ይዘት ባጭሩ፡ አመልካች ጉዳት ያደረሰዉ ተሽከርካሪ ባለንብረት በመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.2081 መሰረት ኃላፊነት ያለበት በመሆኑ፣ አደጋዉ በደረሰበት ወቅት ተሽከርካሪዉን አከራይቼ ስለነበር ኃላፊነት የለብኝም በማለት ያቀረበዉ መከራከሪያ ተቀባይነት የለዉም፤ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.2082 (2) መሰረት ከኃላፊነት ነጻ ሊሆን የሚችለዉ ተሽከርካሪዉን ስለባለንብረቱ ወይም ስለሌላ ሰዉ የያዘ ተቀጣሪ ሰራተኛን እንጂ የተሽከርካሪዉን

ባለቤት ወይም አመልካችን ነጻ የሚያደርገዉ ባለመሆኑ በዚህ ረገድ የቀረበዉ ክርክር ተቀባይነት የለዉም፡፡ አመልካች የጠቀሳቸዉ የሰበር መዝገቦች የተሽከርካሪዉን ባለቤት ከኃላፊነት ነጻ የሚያደርገዉ አይደለም፡፡ በ1ኛ ተጠሪ ደንበኛ ተሽከርካሪ ላይ የደረሰዉ አደጋ አመልካች እና 2ኛ ተጠሪን ባልተነጣጠለ ኃላፊነት የሚያስጠይቅ ነዉ፤ ለእያንዳንዳቸዉ በየደርሻቸዉን ለመለየት የሚያስችል ሕግ ባለመኖሩ የአመልካች ቅሬታ ዉድቅ እንዲደረግለልን በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካች ሚያዚያ 26 ቀን 2015 ዓ.ም በተጻፈ የመልስ መልስ የሰበር አቤቱታዉን በማጠናከር ተከራክሯል፡፡ 2ኛ ተጠሪ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ጥሪ ተደርጎለት ባለመቅረቡ የጽሑፍ መልስ የመስጠት መብቱ ታልፏል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከፍ ሲል የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር አግባብነት ካላቸዉ የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነዉ የ1ኛ ተጠሪ ደንበኛ የሆነዉ መከላከያ ሚኒስቴር ተሽከርካሪ በሆነዉ የሠ.ቁ. 06890 መካ ላይ የግጭጥ አደጋ ያደረሰዉ የሠ.ቁ. ኮድ 3-15499 ኢት የሆነዉ ተሽከርካሪ የ2ኛ ተጠሪ እና የሠ.ቁ.3-03984 ኢት ተሳቢ የሆነዉ ደግሞ የአመልካች ንብረት የሆነዉ መሆኑን በሥር ፍ/ቤት የተረጋገጠዉ ፍሬ ነገር ነዉ፡፡ ነገር ግን የአመልካች ንብረት የሆነዉን ተሳቢ ተሽከርካሪ በ1ኛ ተጠሪ ደንበኛ ተሽከርካሪ ላይ የግጭት ጉዳት በደረሰበት ወቅት የአሁን 2ኛ ተጠሪ ተከራይተዉ ሲገለግለበት በነበረበት ወቅት መሆኑን የሥር ፍ/ቤት የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነዉ፡፡ በ1ኛ ተጠሪ ደንበኛ ተሽከርካሪ ላይ የግጭት አደጋ በደረሰበት ወቅት የአመልካችን ተሳቢ በኪራይ ዉል ተከራይተዉ ለራሱ ጥቅም ሲገለገልበት የነበረ እስከሆነ ድረስ አመልካች በዚህ ጉዳይ ኃላፊነት አለበት ወይስ የለበትም? የሚለዉ ነጥብ መታየት ያለበት ጉዳይ ነዉ፡፡

እንደሚታወቀዉ የአንድ መኪና ወይም የአንድ ባለሞተር ተሽከርካሪ ባለቤት በሌላ ሰዉ ላይ ላደረሰዉ ጉዳት ባለሀብቱ ኃላፊ እንደሚሆን፣ ባለሀብቱ ከዚህ ኃላፊነት ነጻ ሊሆን የሚችል መኪናዉ ወይም ባለሞተር ተሽከርካሪ ጉዳት ባደረሰበት ወቅት የተሰረቀበት መሆኑን የሚያስረዳ መሆኑን ከፍ/ብ/ሕ/ቁ.2081 ድንጋጌ ይዘትና ዓላማ መረዳት ይቻላል፡፡ እንዲሁም መኪናዉን ወይም ባለሞተር ተሽከርካሪዉን ለግል ጥቅሙ ሊገለገልበትና ሊጠቅምበት የወሰደዉ ሰዉ ተሽከርካሪዉ በእጁ እያለ በሚገኝበት ጊዜ ላደረሰዉ ጉዳት ኃላፊ እንደሚሆን በፍ/ብ/ሕ/ቁ.2082 (1) ድንጋጌ ሥር ተመልክቷል፡፡ የመኪናዉ የባለሞተር ተሽከርካሪ ባለቤት ተበዳዩን ከካሳ በኋላ በመኪናዉ ወይም በባለሞተር ተሽከርካሪ ሲገለግልበት ወይም ሲጠቀምበት ከነበረዉ ሰዉ በሲሳራዉ አከፋፈል መጠየቅ እንደሚችል በፍ/ብ/ሕ/ቁ.2083 (1) ድንጋጌ ሥር ተመልክቷል፡፡ በዚህ ረገድ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ.55228 ጥር 25 ቀን 2003 ዓ.ም (ቅጽ 11) በሰጠዉ አስገዳጅ ዉሳኔ አመልካች አቶ አብራር ሳቢር እና በተጠሪዎች 1. ወ/ሮ አለምጸሐይ ወሰኔ እና 2. ጥበቡ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር መካከል በነበረዉ ክርክር የአመልካች ንብረት የሆነዉ መኪና በኮንትራት ለ2ኛ ተጠሪ ተሰጥቶ እያለ በአቶ አብርሃም አክሊል ላይ ላደረሰዉ ጉዳት፣ 2ኛ ተጠሪ መኪናዉን ሲገለገልበት የነበረ መሆኑ ከታወቀ የመኪናዉ አሽከርካሪ ባለንብቱ መቅጠሩ መታወቁ መኪናዉን ሲገለገልበት የነበረን ሰዉ ከኃላፊነት ነጻ ሊያደርገዉ የሚችል ሕጋዊ ምክንያት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ.2082 ድንጋጌ በመሰፈርትነት ያላስቀመጠዉ ነጥብ ነዉ፡፡ በመሆኑም ጉዳቱን ያደረሰዉን መኪና ሲገለገልበት የነበረዉ 2ኛ ተጠሪ መሆኑ ከተረጋገጠ የመጨረሻ ኃላፊቱን [ultimate liability] ሊወስድ የሚገባዉ ይኸዉ ተጠሪ ነዉ በማለት መወሰኑን ማየት ይቻላል፡፡ ከዚህ ዉሳኔ መረዳት እንደሚቻለዉ አንድ መኪና ወይም ተሽከርካሪ በኪራይ ዉል ወስዶ ለግል ጥቅሙ ሲገለገልበት ወይም ሲጠቀምበት የነበረዉ ሰዉ መኪናዉ በእጁ እያለ ጉዳት ያደረሰ እንደሆነ ለደረሰዉ ጉዳት ኃላፊ መሆን እንደሚገባዉ ያመለክታል፡፡

በዚህ መሰረት አሁን ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ የአመልካች ንብረት የሆነዉ ተሳቢ ተሽከርካሪ በኪራይ ዉል ለ2ኛ ተጠሪ ተሰጥቶ፣ 2ኛ ተጠሪ ለግል ጥቅሙ ሲገለገልበት የነበረ በመሆኑ፣ በ1ኛ

ተጠሪ ደንበኛ ንብረት በሆነዉ ተሽከርካሪ ላይ የግጭት አደጋና ጉዳት ያደረሰዉ የ2ኛ ተጠሪ ንብረት በሆነዉ ተሽከርካሪ ላይ ይህ ተሳቢ ተገጥሞ ሲንቀሳቀስ፣ በ2ኛ ተጠሪ እጅ ሆኖ ሳለ የደረሰ ጉዳት በመሆኑ፣ ከፍ ሲል በተጠቀሰዉ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ከሰጠዉ አስገዳጅ የሰበር ዉሳኔ አንጻር፣ ለዚህ ጉዳይ ኃላፊነት ያለበት የአሁን 2ኛ ተጠሪ ብቻ እንጂ አመልካች ከተጠሪ ጋር በአንድነት ኃላፊ የሚሆንበት አግባብ የለም። በመሆኑም በ1ኛ ተጠሪ ደንበኛ ንብረት በሆነዉ ተሽከርካሪ ላይ ለደረሰዉ ጉዳት ኃላፊ መሆን ያለበት የአሁን 2ኛ ተጠሪ ብቻ እንጂ አመልካች ከ2ኛ ተጠሪ ጋር በአንድነት ኃላፊ ሆኖ ጉዳት የደረሰበትን ተሽከርካሪ ለማስጠገን የወጣዉን ወጪ የሚከፍለበት አግባብ ሳይኖር፣ የሥር ፍ/ቤት አመልካች እና 2ኛ ተጠሪ በአንድነት ለተሽከርካሪ ጥገና የወጣዉን ወጪ ለ1ኛ ተጠሪ እንዲከፍሉ በማለት ያሳለፉት ዉሳኔ የሕግ ድጋፍ የለም።

ሲጠቃለል የሥር ፍ/ቤቶች በ1ኛ ተጠሪ ደንበኛ ንብረት በሆነዉ ተሽከርካሪ ላይ ለደረሰዉ ጉዳት የጉዳት ካሳ መክፈል ያለበት የአሁን 2ኛ ተጠሪ ብቻ ሆኖ ሳለ አመልካችም ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ተሽከርካሪዉን ለማስጠገን 1ኛ ተጠሪ ያወጣዉን ወጪ በአንድነት እንዲከፍሉ በማለት የወሰኑት ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ ተከታዩን በአብላጫ ድምጽ ወስነናል።

ዉሳኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ.288007 በ13/3/2014 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.282450 ሚያዚያ 7 ቀን 2014 ዓ.ም የሰጠዉ ብይን መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸዉ ስለሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 (1) መሰረት ተሻሽሏል።
2. የ2ኛ ተጠሪ ንብረት የሆነዉ ተሽከርካሪ እና የአመልካች ንብረት የሆነዉ ተሳቢ በ2ኛ ተጠሪ እጅ እያለ በ1ኛ ተጠሪ ደንበኛ ንብረት በሆነዉ ተሽከርካሪ ላይ ለደረሰዉ የግጭት አደጋ/ጉዳት 1ኛ ተጠሪ ተሽከርካሪዉን ለማስጠገን ያወጣዉን ወጪ መክፈል ያለበት የአሁን 2ኛ ተጠሪ ብቻ ነዉ ብለናል። አመልካች የአሁን 1ኛ ተጠሪ የደንበኛዉን ተሽከርከሪ ለማስጠገን ያወጣዉን ወጪ የሚከፍልበት የህግ አግባብ የለም ብለናል።
3. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ።
4. ግራ ቀኙ የሰበር ክርክር ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ።

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ዐ

ማ ሰታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለማንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

<u>የሀሳብ ልዩነት</u>

እኔ ስሜ በተራ ቁጥር 5 ላይ የተመለከተው ዳኛ አብላጫው ድምፅ 1ኛ ተጠሪ የመድን ሽፋን የሰጠውን ተሽከርካሪ ለማስጠገን ያወጣውን ወጪ የመሸፈን ግዴታ ያለበት ተሳቢውን በኪራይ ውል ወስዶ ለግሉ ሲጠቀምበት የነበረው 2ኛ ተጠሪ ብቻ ሊሆን ይገባል በማለት የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ በማሻሻል በሰጠው ውሳኔ ያልተስማማሁ በመሆኑ ለልዩነት ሀሳቡ መነሻ የሆኑኝን ምክንያቶች እንደሚከተለው አስፍራያለሁ፡፡

በመሰረቱ የአንድ መኪና ባለቤት የሆነ ሰው አደጋውን ያደረሰው ይህን መኪና ለማንቀሳቀስ ወይም ለመንዳት ያልተፈቀደለት ሰው ቢሆንም መኪናው ባደረሰው ጉዳት ልክ ሃለፊ የሚሆነው ባለቤቱ መሆኑ በፍ/ብ/ህ/ቁ.2081(1) መመልከቱና ከዚህ ድንጋጌ በተጨማሪ መኪናውን ለግል ጥቅሙ ወስዶ የሚገለገልበት ሰው ካለ መኪናው በእጁ በሚገኝበት ጊዜ ላደረሰው ጉዳት አላፊ መሆኑ በፍ/ብ/ህ/ቁ.2082(1) መመልከቱ ከዚህም በተጨማሪ የመኪናው ባለቤት ይህንን መኪናውን ወስዶ በግሉ ሲጠቀምበት የነበረውን ሰው በኪሳራው አስፋፊል ላይ ሊጠይቀው የሚችለው ተበዳዩን ተገድዶ ክሳሰ በኃላ መሆኑ በፍ/ብ/ህ/ቀ2083(1) መመልከቱ ተበዳዩ ከመካሱ በፊት የመኪናው ባለቤትና ተሽከርካሪውን ለግሉ ወስዶ ሲጠቀምበት የነበረው ሰው ተጠያቂነት የአንድነትና የነጠላ መሆኑን የህጉ አጠቃላይ መንፈስ መሰረት ያደረገው የህጉ ትርጉም ያሳያል፡፡ በእኔ አረዳድ በሰ/መ/ቁ.55228 የተሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም ተበዳዩ ከተካሰ በኃላ ያለን ሂደት የሚያመለክት በመሆኑ ተበዳዩ ከመካሱ በፊት ላለ ክርክር አግባብነት አለው ብዬ አላምንም፡፡

አሁን በያዝነው ጉዳይም 1ኛ ተጠሪ ጉዳት የደረሰበትን የመድን ሽፋን የሰጠበትን መኪና ከካሰ በኃላ ጉዳት በደረሰበት ደንበኛው እግር ተተክቶ በፍ/ብ/ህ/ቁ.2081(1)፣2082(1) እና 2083(1) መሰረት ክሱን የአንድነትና ነጠላ ተጠያቂነት ባለባቸው አመልካችና 2ኛ ተጠሪ ላይ ክስ የማቅረብ የሰፋ መብት ያለው ከመሆኑ አንጻር ክሱን ይህንን የሰፋ መብቱን ተጠቅሞ ማቅረቡና የስር ፍርድ ቤቶችም ይህንን ተቀብለው በአመልካችና 2ኛ ተጠሪ ላይ የአንድነትና ነጠላ ሀላፊነትን መጣላቸው በአግባቡ ስለሆነ በዚህ የክርክር ደረጃ ማለትም 1ኛ ተጠሪ በቅድሚያ ተከሰው በማስከተልም በአመልካችና 2ኛ ተጠሪ መሃከል ክስ ቀርቦ የመጨረሻው ሃላፊነት በማን ላይ ሊወድቅ ይገባል የሚል ክርክር ባልቀረበበት ለጉዳቱ 2ኛ ተጠሪን ብቻ ሀላፊ ማድረጉ የ1ኛ ተጠሪን በህግ የተሰጠውን ከሁለቱም ወገኖች ፍርድ ያረፈበትን ገንዘብ የማስፈፀም መብቱን የሚያጣብብ የፍ/ብ/ህ/ቁ2081(1)፣2082(1)እና 2083(1) የጋራ ንባብ መሰረት ያላደረገ ነው ብዬ ስለማምን የስር ፍርድ ቤቶች የሠጡት ውሳኔ ሊፀና ይገባል በማለት ከስራ ባልደረባዎቼ በሀሳብ ተለይቼያለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት

መ/ዐ

ማ ሰታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለማንዛቤ አንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም